በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መስከረም ፲ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት

**መግቢያ**

- ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ አንዱ መልዕክታት ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ አሥራ አራቱ በቅዱስ ጳውሎስ የተጻፉ ናቸው። ሌሎቹ ሁለቱ በቅዱስ ጴጥሮስ፣ ሦስቱ በቅዱስ ዮሐንስ፣ አንዱ በቅዱስ ያዕቆብ፣ ሌላኛው አንዱ በያዕቆብ ወንድም በይሁዳ የተጻፉ መልዕክታት ናቸው።
- እነዚህ መልዕክታት በእስትንፋሰ እግዚአብሔር በፈቃዱ የተጻፉ ስለሆኑ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ገብተው ተቆጥረዋል። በቅደም ተከተላቸው መሠረት አስቀድመን የቅዱስ ጳውሎስን መልዕክታት እንመለከታለን።
- ጳውሎስ ዕብራዊ ስሙ ሳውል/ሳኦል ሲሆን ትርጉሙም በልመና የተገኘ ማለት ነው። ሳውል/ሳኦል የኪልቅያ አውራጃ በምትሆን ጠርሴስ በምትባል ከተማ ተወለደ። *የሐዋ 22፡3።* ጠርሴስ የሕግና የፍልስፍና ት/ቤቶች ይገኙባት ነበር። ሳውል ከነዚህ ት/ቤቶች የሚገኘውን ትምህርት ቀስሞ ነበር።
- ቅዱስ ጳውሎስ ታላቅ አእምሮ፣ የማስተዋልም ችሎታ የነበረውና ለትምህርትም ጥልቅ ፍላጎት ያለው ነበር። ወላጆቹም በልጅነቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወስደው ለታላቁ የሕግ መምህር ለገማልያል ሰጥተው በአይሁድ የአስተዳደግ ሥርዓት አሳድገውታል። *የሐዋ 5፡34።*
- አይሁድ ልጆቻቸውን ከትምህርት ጋር ዕደ ጥበብ ያስተምሩ እንደነበር ጳውሎስም ከቀለም ትምህርቱ ጋር ድንኳን የመስፋት ሥራን ተምሮ ነበር።
- ቅዱስ ጳውሎስ ለአይሁድ ትምህርት ቀናተኛ ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ የክርስትናውም ትምህርት በሰፊው ተስፋፍቶ ነበር።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት

**መግቢያ**

- ክርስቲያኖችም ከጳውሎስና ከአይሁድ ጥላቻ የተነሳ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ ልዩ ልዩ ከተሞች ይሰደዱ ነበር፡፡ *ገላ 1፡13-14፡፡*
- በእስጢፋኖስ ሞት የተበተኑ ክርስቲያኖች ብዙዎችን ሰዎች በማጥመቅ ክርስቲያኖች እያደረጉ መሆኑን ጳውሎስ ሲሰማ ክርስቲያን የሆኑትን ወንዶችንም ሴቶችንም ለማሰር የሚያስችለው ፈቃድ ወሰደ፡፡
- ወደ ደማስቆ በር ሲደርስም ድንገት ከሰማይ በወረደ መብረቅ ተመትቶ ወደ ደማስቆ ገብቶ ሦስት ቀን ምግብ ሳይበላ ውሃ ሳይጠጣ ቆይቶ ቁጥሩ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት የሆነው ሐናንያ አጠመቀው፡፡ በተጠመቀም ጊዜ ዓይኑ በራለት ምስጢርም ተገለጠለት መንፈስቅዱስም አደረበት፡፡ ሳይውል ሳያድርም ላዲሱ ሃይማኖት ቀናተኛ ሆኖ ልዋል ልደር ሳይል ዕለቱን ማስተማር ጀመረ፡፡
- የጳውሎስንም ክርስቲያን መሆንና ብዙዎችንም ማጥመቁን የሰሙ አይሁድ አዝነው በደማስቆ በር ሲጠብቁ ክርስቲያኖች ግን በመስኮት በኩል በቅርጫት አድርገው አሹልከው ሰደውታል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ የሚሰብክባቸው ቦታዎች ሕዝብ የሚበዛባቸው የሚገኙባቸው ከተሞች ነበሩ፡፡ ከእነርሱም ኤፌሶን፣ አንጾኪያ፣ ተሰሎንቄ፣ ቆሮንቶስ፣ አቴና፣ ሮም፣ ይጠቀሳሉ፡፡
- ሲያስተምርም በምኩራብ፣ በአደባባይ፣ በገበያ፣… ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በትምህርቱ አሳምኖ ያጠመቃቸው እጅግ ብዙ ነበሩ፡፡ በቃል ካስማራቸው ይልቅ በመልዕክቱ ያሳመናቸው ብዙ ናቸው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሁሉ በእጁ እየሠራ ራሱንም ሰዎቹንም ይረዳ ነበር እንጂ ሰዎችን አስቸግሮ ከሰው ገንዘብ ወስዶ አያውቅም፡፡ ብዙ ጊዜ ታስሯል፣ ተደብድቧል፣ እየተከሰሰም መከራ ተቀብሏል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

- የመልዕክቱ ጸሐፊ ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡
- የጻፈበት ቦታ ቆሮንቶስ ነው፡፡
- የጻፈበት ዘመን ከ57-58 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በሦስተኛው ጉዞ ወቅት ነው፡፡
- በበዓለ ጰንጠቆስጤ ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱ መንገደኞች የምስራቹን ወይም በኢየሩሳሌም የሆነውን ዜና ይዘው ወደ አገራቸው ተመልሰው ነበር፡፡
- በቅዱስ እስጢፋኖስም ሞት ከተበተኑት ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ ወደሮም ሄደው ወንጌሉን ወይም የምስራቹን ሰብከው ነበር፡፡
- ከእነዚህም የመጀመሪያዎቹ የሮም ክርስቲያኖች መካከል ከአይሁድ ጋር በቀላውዴዎስ ቄሳር ከሮም የተባረሩት አቂላና ጵርስቅላ የሚገኙ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ በሁለኛው ጉዞው በቆሮንቶስ አግኝቶአቸዋል፡፡
- አቂላና ጵርስቅላም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ወደ ኤፌሶን ተጉዘው በዚያ ከሚገኙት ጋር ስለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስፋት የሚገባውን ሠርተው ወደ ሮም ተመልሰው በሮም በምትገኘው ቤታቸው ቤተ ክርስቲያንን መስርተዋል፡፡ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም፤በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ ሮሜ 16፡3-5፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

*መግቢያ*

- በሮሜ ምዕራፍ 16 ላይ በቅዱስ ጳውሎስ ከቀረበው ሰላምታ እንደምንረዳው በሮም ክርስቲያኖች የሚገናኙባቸው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በየምዕመናኑ ቤት ነበሩ፡፡ *ሮሜ 16፡5፡14፡15፡፡*
- ከእያንዳንዳቸውም ስም እንደምንረዳው እነዚህ ወደ ክርስትና የመጡት የሮም ሰዎች ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ ከአሕዛብ ወገን የመጡ ነበሩ፡፡
- ፍጹም እምነታቸውና ታማኝነታቸው ታውቆላቸው በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች ስማቸውና ክብራቸው እጅግ የገነነ ሆኖላቸው ነበር፡፡
- ከዚህም የተነሳ ቅዱስ ጳውሎስ የሚበልጠውን የክርስትና በጎ ፍቅር ሊያሳድርባቸው ከእነርሱም ሕይወት በጎውን ሊቀስምና ወደ ስፔንም በሚያደርገው ጉዞ ይረዱት ዘንድ አስቦ ብዙ ጊዜ ሊጎበኛቸው ናፈቀ፡፡
- ይህን መልዕክት ቅዱስ ጳውሎስ የላከበት ምክንያት በሮም ጥቂት ጊዜ ወንጌልን ሊሰብክና በዚያም ወደስፔን ለመሻገር ቢያስብም ከአይሁድ ወገን የሆኑት መምህራን ያስፋፉት የነበረው ኑፋቄ በአንጾኪያ በቆሮንቶስና በገላትያ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ከማወክ አልፎ ወደ ሮም መዛመቱ ነበር፡፡
- ይህንኑ ኑፋቄ ለማስወገድና ወደ ሮም ተጉዞ ደስ የሚያሰኝ ቆይታ ለማድረግ የእግዚአብሔርን ወንጌል ምንነት ገልጦ እውነተኛውን ነገር ጻፈላቸው፡፡
- በመልዕክቱም የጌታችን ወንጌል አይሁድም ሆኑ አሕዛብ የሚጎድላቸውን እውነት እንዴት አድርጎ እንደያዘና ይህም ወንጌል የነበረውን ሃይማኖት ክርስትና ያደረገው መሆኑን ገልጾላቸዋል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ**

- ይህም መልዕክት በሮም ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ ከመስጠቱም በላይ ወንጌሉን በማጣመም ለሚተረጉሙትም ሆነ ወንጌሉ በራሱ በቂ አይደለም ብለው ያምኑ ለነበሩት ለአንዳንዶች የሚሆን ምላሽ የሰጠ ነው።
- መልዕክቱም የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ኃይል የሚያምኑትን እንዴትና ለምን እንደሚጠብቃቸው ይተነትናል።
- በመልዕክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ አከፋፈል እንደሚከተለው ነው፡-
    - የጸሐፊው ማንነት (1፡1-5)
    - መልዕክቱ የተጻፈላቸው እነማን እንደሆኑ (1፡6-15)
    - ወንጌሉና የስብከታቸው ፍሬ ነገር (1፡16-17)
    - አሕዛብና መዳን ለነርሱ ስለማስፈለጉ ((1፡18-32)
        - እግዚአብሔርን ያላከበሩት በደለኞች (1፡18-23)
        - በበደለኞች የተቆጣ ቅዱስ እግዚአብሔር (24-32)

# <u>የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች</u>

## የመልዕክቱ ጸሐፊ (ሮሜ 1፡1-5)

- የመልዕክቱ ጸሐፊ ጳውሎስ ነው፡፡ ዕብራዊ ስሙ ሳውል (ሳኦል) ነው፤ ትርጉሙም በልመና የተገኘ (ዘተስእለ) ማለት ነው፡፡ ከነገደ ብንያም በጠርሴስ የተወለደ አይሁዳዊ ነበር፡፡
- ሐዋርያ እንዲሆንም በእግዚአብሔር ስለተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ በማለት ስለራሱ ተናግሯል፡፡ *<u>ሮሜ 1፡5፣ 1፡1-2፡፡</u>* ይህ ሐዋርያ ይሆን ዘንድ የተሾመ የተቀባ ነበር፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌል የመዳናችን የምስራች (ዜና) እንደሆነ ጽፎልናል፡፡
- ወንጌሉም ዓለሙን ሁሉ ሊያድን የወደደ የእግዚአብሔር ወንጌል ነው፡፡
- እግዚአብሔር ስለዚህ መዳናችንም በብሉይ ቃል ገብቶልናል፡፡ቃል ኪዳኑም የባሕርይ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ከዳዊት ዘር በመወለዱ ወይም ሰው በመሆኑ፤ መከራ ተቀብሎ ስለሰው በመሞቱ
- እግዚአብሔር ወልድ ለአባቱ የባሕርይ ልጁ መሆኑም በትንሣኤ ሞት ሳያሸንፈው በመነሳቱም ተረጋግጧል፡፡ እርሱ ቅዱስ ስለሆነ ሞት አላሸነፈውም፤ ሞት የኃጢአት ደመወዝ ነውና፡፡
- ጌታችን አምላካችን ለሰው ዘር ሁሉ በፈጸመው በዚህ ማዳኑ ቅዱስ ጳውሎስ ጸጋን ተቀብሎ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ ተመርጧል፡፡
- የእግዚአብሔር ጸጋው ቅዱስ ጳውሎስን ፈጽሞ ይለወጥ ዘንድ ታላቅ ነገርን አድርጓል፡፡
- ሃይማኖት የአምላካችን የእግዚአብሔር (የመለኮት) መገለጥ ነውና በፍጹም መታዘዝ ልንቀበለው ይገባል፡፡ የምንቀበለው ጸጋና አገልግሎትም ለእግዚአብሔር ለስሙ ክብር እናደርገው ዘንድ የሚሰጥ ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መልዕክቱ የተጻፈላቸው (ሮሜ 1፡6-15)**

- ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሮማውያን በመንፈስቅዱስ የመዳኑን ጸጋ እንዲቀበሉ ተጠርተዋል፡፡
- እነዚህም በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ማመን ከኃጢአት ነጻ በማድረግ ለቅደስና የሚያበቃ ነውና ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ የተጠሩ በእግዚአብሔር የተወደዱ ነበሩ፡፡
- ጸጋ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው፤ ሰላምም የዚህ ስጦታ ፍሬ ነው፡፡
- እነዚህ ሀብታት ወይም ስጦታዎች ከባሕርይ አባቱ ከአብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመንፈስቅዱስ ተሰጥተውናል፡፡
- መልዕክቱን በበጎ ነገር የሚጀምር ቅዱስ ጳውሎስ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ስለተሰማች የቀናች ሃይማኖታቸው በማመስገን መልዕክቱን መጻፍ ጀምሯል፡፡
- በእኛ ያለ መልካምነት ሁሉ የተገኘበትን እግዚአብሔርንም አመስግኗል፡፡
- በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት የቻልነው በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተነሳ ነው፡፡ ‹‹አምላኬ›› የሚለውም ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ዝምድና የሚያመለክት ነው፡፡
- በመንፈስ የሆነ እውነተኛ አምልኮ በመንፈስቅዱስ የሚመራ ነው፡፡ ይህ አምልኮትም ወንጌልን መስበክም ነው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ እንደ አባት እንዲሁም እንደ ካህን ሳይታክቱ ስለሕዝቦቹ የመጸለይን ቀዳሚ ኃላፊነቱን አልዘነጋም ነበር፡፡ ለዚህም ጸሎቱን የሚቀበል እግዚአብሔር ምስክሩ ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መልዕክቱ የተጻፈላቸው (ሮሜ 1፡6-15)**

- ቅዱስ ጳውሎስ የሮም ምዕመናንን ሊጎበኛቸው መሻቱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ በመስጠት ገልጦታል፡፡
- ሊጎበኛቸውም መመኘቱ የመነጨው ከመንፈሳዊ ስጦታዎቹ ለእነርሱ በማካፈል በመንፈሳዊነት ለማነጽ ከመፈለጉ ነበር፡፡
- ይህ የመንፈስቅዱስ ስጦታ ከአይሁድ የክህደት ትምህርትና ከአሕዛብ ከንቱ መመካት የሚጠብቃቸው መሆኑንም ነግሮአቸዋል፡፡
- በአገልግሎት አገልጋዮችም ሆኑ ምዕመናኑ አንድ በሆነ ሃይማኖታቸው እርስ በርስ ይተጋገዛሉ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ የእርሱ ሃይማኖት እነርሱ እየተከተሉ ከሚገኙት የማይገባ ነገር የጸዳ መሆኑን ፍንጭ በመስጠት ሊያርማቸው መፈለጉን ጠቁሟቸዋል፡፡
- ሊጎበኛቸው ወደ ቢጸልይም አለመቻሉን አስመልክቶ ጊዜው እስኪሆን ወይም እስኪደርስ በትዕግሥት መጠበቅ እንደሚገባ መከራቸው፡፡
- በአይሁድ የክህደት ትምህርትና በአሕዛብ ከንቱ ትምህርት የተበረዘ እምነታቸውና በማጥራት እርሱን መምሰላቸው መልካም ፍሬ መሆኑን ገልጧል፡፡
- ስላለበትም ዕዳ፡ በእግዚአብሔር ስጦታ የተነሳ ሁሉን መውደድና በሕይወትም ሁሉ ፈጽሞ መለወጥ እንደሚገባ ጻፈ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## መልዕክቱ የተጻፈላቸው (ሮሜ 1፡6-15)

- ግሪኮችን ጥበበኞች እንዲሁም ያልተማሩትን (ባርባርያውያንን) ሳይቀር በሚቻለው ሁሉ በተሰጠው ስጦታ፣ በፍጹም ቅንዓትና ትዕግሥት የሚመጣውን መከራ ሁሉ በመታገስ ወንጌልን በመስበክ በእምነታቸው (በሃይማኖታቸው) የተገኘባቸውን ሕጸጽ እንደሚያርምና በዚህም እንደሚጸና ጻፈ፡፡
- በሮም ላሉትም ስለተሰቀለው ስለክርስቶስ በኃይል ለሚያምኑ ሮማውያን ማስተማር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ አውቃለሁ አላቸው፡፡

## ወንገል (ሮሜ 1፡16-17)

- ቅዱስ ጳውሎስ አህዛብ በተሰቀለው ክርስቶስ ለማመን የሚቸግራቸው ቢሆኑም የክርስቶስን ወንጌል በመስበኩ እንደማያፍር ገልጧል፡፡ ምክንያቱም መጽሐፉ የሞራል ሳይሆን የሚያምኑበትን ሁሉ ወደ መዳን የሚያደርሳቸው የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፡፡
- በቅደም ተከተል ሲቆጠር አይሁድ አስቀድመው መጥተዋል፤ በወንጌል በእግዚአብሔር የሆነ ጽድቅ እንዴት እንደሚገኝ እናውቃለን፤
- የመጀመሪያውም ደረጃ ማመን ነው፡፡ እምነትም ለቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ብቁ ያደርገናል፤ ጽድቃችንማ በዚሁ ነው በእርሱም ይፈረድልናል፤
- ይህም እምነት በምንሠራው ሥራ ያድጋል፤
- እድገትም የሕይወት ምልክት ነው፤ ሕይወት የሌለው ነገር አያድግም በማለት ነግሮአቸዋል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**ወንጌል (ሮሜ 1፡16-17)**

- ጻድቅ በእምነቱ በሕይወት ይኖራልና፡፡ *ዕን 2፡4፡፡*
- ይህም እምነት በእግዚአብሔር ምሕረት፣ ፍቅር፣ ማዳን፣ ኃይል ያለን ጽኑ እምነት ነው፡፡

**አሕዛብ መዳን የሚያሻቸው መሆናቸው (ሮሜ 1፡18-32)**

- ሰው ከእግዚአብሔር በመለየቱ፣ በመበደል ከጽድቅ በመራቁ የተነሳ ለጽድቅ ታላቅ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ይህም በደል የእግዚአብሔርን ቁጣ ቀስቅሶ ነበር፡፡
- ሰው ተመርቶባት ወደ እግዚአብሔር ረድኤት ለመቅረብ እውነትን ባይጠቀምባትም እውነት ግን ከውድቀቱ ጀምሮ በሕይወቱ ውስጥ የቀረች ብርሃን ነበረች፡፡
- የሰው ምክንያተኝነቱ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ስለበደለው በደሉ አስወቅሰው እንጂ አልጠቀመውም
- ስለእግዚአብሔር ያውቁ ዘንድ የተገለጠላቸውን እውነት ስላላመኑ ይቅርታን አያገኙም፡፡
- *በሮሜ 1፡20* እንደተገለጠው ስለእግዚአብሔር በሁሉ ይታወቅ ዘንድ የሚገባው ተገልጧል፡፡
- እግዚአብሔርን አናየውም ነገር ግን በሥራው እግዚአብሔር እንደሆነ እናምነዋለን እንጂ፡፡
- አሕዛብ ግን እግዚአብሔርን በሚገባው ክብር አላከበሩትም በዘላለማዊ ኃይሉ የሚሰጠውንም አገልግሎት አልሰጡትም፡፡ ሰዎች በፈቃዳቸው ከእውነት ሲለዩ ወደ ሚበልጥ አደገኛ ስህተት ያመራሉና፡፡
- በክህደት ዓለም በባዕዳን አማልክት አምልኮ የሚኖሩ እነዚህ ሰዎች ስተው ሕዝቡም በጥልቅ ጨለማ ተይዘው ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## አሕዛብ መዳን የሚያሻቸው መሆናቸው (ሮሜ 1፡18-32)

- ግሪኮችና ሮማውያን በጥበባቸው ተመክተው የተቀረውን ዓለም ሁሉ ባለመታዘዝ ሲመሩት ይህ የጣዖት አምልኮታቸው ፍጹም ሞኝነታቸውን ገልጦባቸው ነበር፡፡ በእውነተኛው አምላክ በእግዚአብሔር ሌሎች ባዕዳን አማልክትን ተክተው አምልከዋልና፡፡
- ስለዚህ ድንቁርናቸው ስለመረጡት የድንቁርና መንገዳቸው ለሚብስ የድንቁርና አሠራርና ለተዋረደ ሞራላዊ ውድቀት አሳልፎ ሰጣቸው፡፡
- ሃይማኖታቸው በገዛ ሰውነታቸው የሚሠሩትን ኃጢአት ለመረዳት አልረዳቸውም ነበር፡፡
- እጅግ በሚያስነውርና በተናቀው ኃጢአት ተይዘው ተገኙ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ግን በዘመኑ የነበረውን በኢአማንያን የተጻፈውን ጥቂቱን በመጥቀስ ጻፈልን እንጂ በአሕዛብ ዓለም የደረሰውን የሕይወት ብክለት ቋንቋ ሊገልጠው የሚከብድ ነበር፡፡
- የማይታየውን የእግዚአብሔርን ክብር ለፈጣሪያቸው ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለፍጡራን ጣዖታት አምልኮት አሳልፈው ሰጡ፡፡
- አስቀድሞ የተለያዩ ቅርጾች አንድን ነገር ለመወከል የሚሠሩ ነበሩ ቆይተው ግን ቅርጾቹን የአምልኮት መሣሪያ አደረጓቸው፡፡
- እግዚአብሔርም ራሳቸውን እንዲያዋርዱ ለፍትወታቸው አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም ሰው ያለ እግዚአብሔር ሲኖር የሚወድቅበትን ጥልቅ አወዳደቅና ነገር የሚጠቁም ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## አሕዛብ መዳን የሚያሻቸው መሆናቸው (ሮሜ 1፡18-32)

- አሁን ለመግለጽ የሚከብደንን እጅግ የበዛ ፍትወትነ ሳያፍሩ በስሜት ፈጸሙ፡፡ ይህ እግዚአብሔርን በማያምኑ መካከል የሚገኝ ነው፡፡
- የጥንቱ የሰዶማውያን ግብር በመጀመሪያይቱ መቶ ክፍለ ዘመን በሮማውያን ዘንድ የተለመደ ነበር፣ በጸሐፊዎቻቸውም አማካይነት ያለሐፍረት ተጽፏል በአንደበታቸውም ተነግሯል፡፡
- ይህም የአሕዛብ ግብራቸው በሃይማኖታቸውም ሆነ በሕጋቸው የተከለከለ አልነበረም ይልቁኑ ያለማፈር ተቀባይነት አግኝቶ ይኖር ነበር እንጂ፡፡
- ስለስህተታቸውም በተቀበሉት ቅጣት ለሚያስነውር ኃጢአት ተላልፈው ተሰጡ፡፡
- ከእውነት ራሱን የሚለይ ሁሉ የራሱን መንገድ ለመምራት አይከለከልም፡፡ በዚህ መንገዱ ግን ከጥልቁ ወደሚብሰው የስህተት ጥልቅ እየገባ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን በመምረጡ የሚበዛውን የክፋት አረም (እንክርዳድ) ያመርታል፡፡
- የማይገባ አእምሮ እግዚአብሔርን ይክዳል፡፡ ይህም አእምሮ፡-
  - ለራሱ የሚያገኘው ጥቅም ባይኖርም ሌላውን ለመጉዳት የሚነሳሳና የሚጎዳ ነው፡፡
  - በምስጢር ሌሎችን ለማዋረድ ድምጻቸውን ሳያሰሙ ይመከራል፡፡
  - ከሌሎች ጀርባ ሆኖ ይናገራል ስም ያጠፋል፡፡
  - እግዚአብሔርን ይጠላል፣ ጥበቃውን ይክዳል፣ ፈታሒነቱንም ይቃወማል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**አሕዛብ መዳን የሚያሻቸው መሆናቸው (ሮሜ 1፡18-32)**

- **የማይገባ አእምሮ እግዚአብሔርን ይክዳል። ይህም አእምሮ፡-**
  - ክፋትን ይፈላለጋል፣ ይህን አዳዲስ ደስታን ይሰጠዋዋል፣እርሱም አዲስ የጥቅም መስመር እንደሆነ ያስበዋል፣ በተለይም በጦርነት ሌሎችንም ለመጉዳት ይጠቀሙበታል።
  - ፍቅር የሌላቸው፣ የገዛ ልጆቻቸውን በብርድ፣ በረሐብ ወይም በጫካ አውሬዎች እንዲበሉ አሳልፈው ይሰጣሉ።
- እነዚህም በእግዚአብሔር ፍርድ ይቀጣሉ። ይህንም ቅጣት ፈላስፎች የተፈጥሮ ሕግ ብለው ይጥሩት እንጂ ይህም በበደለኛነት የመኖር የመጨረሻው ደረጃ ነው።
- ሰው በውስጥ ስሜቱ የሚጠላውን ለማድረግ የሚፋጠን ከሆነ፤ ይህ ሰው ክፋትን በሚያደርጉ የሚደሰትና መበደልም የሚወድ ነው። ይህም ሰው ከራሱ አልፎ ሌሎች ኃጢአት እንዲሠሩ እያነሳሳ የሌሎችንም የኃጢአት ክምር በራሱ ያኖራል።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**ማጠቃለያ**

- ሐዋርየው ቅዱስ ጳውሎስ ራሱንና ጥሪውን የገለጠው እንዴት ነው?
- በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለው ግኑኝነት ምንድር ነው?
- ጌታችን አምላካችን የሰው ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሁም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አስታራቂ ነው የሚለውን ቅዱስ ጳውሎስ ያብራራው እንዴት ነው?
- ቅዱስ ጳውሎስን ከመልዕክቱ ጋር የሚያገናኘውን መንፈሳዊ ማሠሪያ ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን ከመጻፉ በፊት ሮምን ጎብኝቶ ነበር? መልሳችንን በምን ልናስረዳው እንችላለን?
- እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አገላለጽ የጌታችን ወንጌል አስፈላጊነት ምን ያህል ነው?
- እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን ባለማወቅ የተነሳ የሚሰጥ ይቅርታ አለ? ግለጹ፡፡
- በሮም የነበሩ ጣዖታትን ያመልኩ የነበሩ ሕዝቦች ይሠሩት የነበሩትን ኃጢአቶች እና፤ ከእግዚአብሔርም የተቀበሉትን የቅጣት ዓይነት ግለጹ፡፡
- እግዚአብሔር ጣዖታትንና አምላኪዎቹን ዝም የሚላቸው ስለምንድር ነው?

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org